# ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም

# ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቀርብ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ1998 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት

# እና የ1999 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር እቅድ አፈፃፀም

## አጭር መግለጫ

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባዔ
የተከበሩ ም/አፈጉባዔና
የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!
ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101/2 በመመሥረት መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 8 በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 94/2 መሠረት የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የኘሮግራምና የአሠራር ቅልጥፍና ምርመራ ወይም ክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣ ያከናወነውን የምርመራ ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቱ እና ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት

የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲጓብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፣

- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚጓብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፡፡

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ናቸው፡፡

በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀጽ (1) መሠረት ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ተግባራት በተመለከተ ስለተከናወነው የኦዲት ሥራና ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አጠቃላይ ዓመታዊ ዘገባ እንደሚቀርብ የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የመ/ቤቱ ሪፖርት ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፣

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፣ ለክልሎች የተሰጠ የድጋፍና ልዩ ድጎማ ሂሣብ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት፣ የክዋኔ እና ልዩ ኦዲት ሪፖርቶችን የያዘ ነው፡፡

2. መሥሪያ ቤቱ ባለበት የባለሙያ እጥረት ምክንያት አብዛኞቹ በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኦዲት በመንግሥታዊ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች የተመረመሩትንም የኦዲት ሪፖርት ያካትታል፡፡

3. ስለሆነም፣ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የሚቀርቡት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር የ1998 የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የ1999 ያለፉት ዘጠኝ ወራት ክንውኖች፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች፣ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም የተከናወኑ

ተግባራት፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ይዞታ እና የኦዲት አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው::

4. በ1998 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ ጥራዞች ለም/ቤቱ የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲችል በጥልቀት የተዘጋጁ ሲሆን የሪፖርቶቹም ቅጅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲደርስ ተደርጓል::
5. እያንዳንዱ ኦዲት እንደተፈጸመ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መልስ የሰጡ 65 መ/ቤቶችን አስተያየት ያገናዘበ ሲሆን፣ ለመ/ቤታችን መልስ ያልሰጡ 95 መ/ቤቶች በላክነው ሪፖርት እንደተስማሙ በመቁጠር የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል::
6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ መንግሥት ሂሣብ ኦዲት ደረጃዎች፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፣ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው::

## <u>የ1998 በጀት ዓመት ዕቅድና ክንውን</u>

7. መ/ቤቱ ባለው ውሱን ድርጅታዊና የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅም በ1998 በጀት ዓመት በመደበኛ የፋይናንሻል ኦዲት 187 ሂሳቦችን ኦዲት ለማድረግ አቅዶ 160 መደበኛና ስድስት ልዩ ኦዲቶችን እንዲሁም የ1996 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት አከናውኗል:: ይህም ከዕቅዱ 90% እንደተከናወነ ያሳያል:: ይህ አፈፃፀም ከ1997 ጋር ሲነፃፀር በ8 ኦዲት ወይም በ5% ዕድገት ማሳየቱን ያመለክታል:: በበጀት ዓመቱ የታቀደው በተጠቀሰው መልክ ሊከናወን የቻለው የመ/ቤቱ ሠራተኞች በአዲሱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ውጤቶች ላይ ግንዛቤ በማኅልበት የሥራ ተነሳሽነት በመፈጠሩ ነው::
8. በመንግሥት የተቀረጹ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውንና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና

ስኬታማነት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ (Performance) ኦዲት ያከናውናል:: በዚህ መሠረት በሁለት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትና አንድ የአካባቢ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱም በ1998 በጀት ዓመት ለም/ቤቱ ቀርቧል::

## የ1998 በጀት ዓመት የበጀት አፈጻጸም

9. በ1998 በጀት ዓመት ለመ/ቤቱ የተፈቀደውና የተስተካከለ በጀት ለደመወዝና አበል ብር 5,749,586.40፣ ለሥራ ማስኬጃ ብር 2,949,067.16 በድምሩ ብር 8,698,653.56 ነው:: ከዚህ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው ብር 7,681,901.78 ወይም ከበጀቱ 88% ሲሆን፣ ሳይሰራበት የተረፈ በጀት ብር 1,016,751.78 ወይም 12% ሆኗል:: ካልተሰራበት በጀት ውስጥ ከፍተኛው ለደመወዝ የተመደበው ሲሆን፣ በተፈቀደው የመ/ቤቱ መዋቅርና የደመወዝ እስኬል መሠረት ብቁ ባለሙያዎችን አወዳድሮ መቅጠር ስላልተቻለ፣ እና ከመ/ቤታችን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ የ27 ሠራተኞችን ተመላሽ ደመወዝ ይጨምራል::

## የመ/ቤቱ የ1999 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም

### የኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም

10. መ/ቤታችን በ1999 በጀት ዓመት በመደበኛ ኦዲት 280 ሂሣቦችን ኦዲት ለማከናወን አቅዶ ባለፉት 9 ወራት በመደበኛ ኦዲት የ158 ሂሣቦች ኦዲት ሲጠናቀቅ /የ1997 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪን ሂሳብ ጨምሮ/ 74 ኦዲቶች በመከናወን ላይ ይገኛል:: ይህም በአጠቃላይ የተጠናቀቁትና በመከናወን ላይ ያሉት 232 (82.8%) ኦዲቶች ሲሆኑ፣ በክዋኔ ኦዲት ደግሞ ሁለት የአካባቢ ኦዲቶች፣ ሁለት የደሰሳ፣ ሁለት የቅኝት እና በሶስት መ/ቤቶች የዝርዝር የኦዲት ሥራ ማከናወን እንዲሁም ካለፈው ዓመት የዞሩ የሁለት መ/ቤቶችን ሪፖርት ማዘጋጀት ዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሁለት የአካባቢ ኦዲቶችና አንድ የክዋኔ ኦዲት በመከናወን ላይ ሲሆኑ ሁለት የክዋኔ ኦዲቶች ደግሞ ዝርዝር የኦዲት ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሚመለከተው መ/ቤት ተልኳል:: በተጨማሪም አንድ የክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ በክለሳ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ አንድ የደሰሳ ሥራ ተጠናቆ በሌላ አንድ መ/ቤት ላይ የደሰሳ ሥራ በመከናወን ላይ ነው:: በአጠቃላይ የመ/ቤታችን የዘጠኝ ወራት የእቅድ አፈፃፀም ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር (82.8%)

ስለሆነ በ4ኛው ሩብ አመት ላይ ብዙ ኦዲቶች ስለሚጠናቀቁ የዘመኑ እቅድ አፈፃፀም የተሻለ እንደሚሆን ይጠበቃል።

## የመሰረታዊ አገልግሎት ማስከበር (PBS) ተከታታይ ኦዲት

11. ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር (PBS) የአለም ባንክ የሰጠው ድጋፍ ኦዲት እየተደረገ የኦዲት ሪፖርቱን ለእርዳታ ሰጪው ድርጅቶች ለማቅረብ መንግሥት በገባው የውል ግዴታ መሠረት መ/ቤታችን በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ በመንቀሳቀስ በናሙና በተመረጡ ወረዳዎች ላይ የተከተተይ ኦዲት በማከናወን ላይ ይገኛል።

በዚህም መሠረት፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሩብ ዓመት ኦዲት የተደረጉ 119 ወረዳዎች ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከ ሲሆን፣ የ69 ወረዳዎች የኦዲት ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ በክለሳ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ይህ ሪፖርት እስከቀረበበለት ጊዜ ድረስ የ20 ወረዳዎች ሂሣብ የኦዲት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

## የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

12. በ1989 ዓ.ም በጸደቀው የመ/ቤቱ መዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለቴክኒክ ባለሙያ 285 እና ለድጋፍ ሰጪ 177 በድምሩ 462 ናቸው። በያዝነው በጀት ዓመት ያለፉት ዘጠኝ ወራት 7 የኦዲት ባለሙያ እና 10 የድጋፍ ሰጪ አዲስ ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 13 የኦዲት ባለሙያዎች እና 4 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መ/ቤቱን በልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ በመሆኑ ባሁኑ ጊዜ የሚገኘው የሠራተኛ ብዛት 185 ኦዲተር እና 148 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ ናቸው። ከዚህ ውስጥ 139 (45%) ሴቶች ቀሪው 194 (55%) ወንዶች ናቸው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ድጋፍ ሰጭው ሠራተኛ ከባለሙያ ጋር በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ከፍተኛ ብዛት ያለው መሆኑን ነው።

ለድጋፍ ሰጪው ሠራተኛ የተፈቀደው የደመወዝ ስኬል አነስተኛ ስለሆነ ከፍተኛ ክህሎት (Skill) ያለውን የሰው ኃይል ሊስብ አልቻለም። በመሆኑም ሥራው አነስተኛ ደመወዝ በሚያገኙ ቁጥራቸው የበዛ ሠራተኞች እንዲሸፈን ማድረግ የግድ ሆኗል።

## የበጀት አፈፃፀም

13. ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው በጀት ብር 11.8 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሥራ ላይ የዋለው ብር 5.1 ሚሊዮን ወይም 43% ሲሆን፣ ያልተሠራበት ብር 6.2 ሚሊዮን ነው:: የበጀት አፈፃፀሙ ዝቅ ብሎ ሊታይ የቻለው የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር (PBS) ኦዲት ከአለም ባንክ የተገኘ ድጋፍ አማካኝነት በመከናወኑ አምስቱም ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በመንግሥት የተመደበውን የሥራ ማስኬጃ በጀት ባለመጠቀማቸው፣ በተፈቀደው የመ/ቤቱ መዋቅርና የደመወዝ እስኬል መሠረት ብቁ ባለሙያዎችን አወዳድሮ መቅጠር ባለመቻሉ በበጀት ዓመቱ የለቀቁትን 17 ሠራተኞች ተመላሽ ደመወዝ የሚጨምር በመሆኑ ነው::

## የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም አፈፃፀም

14. በመንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በአገር አቀፍ ደረጃ ተነድፎ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም መ/ቤታችን ከመደበኛ ሥራው ጋር አቀናጅቶ ለመተግበር በ1999 በጀት ዓመት አምስቱን ንዑስ ኘሮግራሞች አቀናጅቶ መተግበር፣ በ1998 በጀት ያልተጠናቀቁ ሥራዎችን ማጠናቀቅ፣ የውጭ ኦዲት ቀሪ ሥራዎችን ማጠናቀቅ፣ የተጠናቀቁ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ (BPR) ጥናቶችን መከለስ እና በIT እንዲደገፉ ማድረግ፣ BPR ባልተሰራባቸው የሥራ ክፍሎች ጥናት ማድረግ፣ የBPR ጥናት የሚያስከትለውን የመዋቅር ለውጥ ተግባራዊ ማድረግ፣ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ምዘና ለመዘርጋት የሚያስፈልጉ ስልጠናዎችን ማግኘትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የመነሻ ዳታ (Baseline Survey) ለመመስረት መረጃ ማሰባሰብ፣ የመነሻ ማነፃፀሪያ ከተመረጡ አገሮች የአሰራሩ ልምድ መሰባሰብ እና ሌሎች ተግባራት በእቅድ የተካተቱ ሲሆን፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ቀጥሎ የተመለከቱት ተግባራት ተከናውነዋል::

- በመ/ቤቱ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ለሥራ አመራር አካላት በ"Leadership development and Transformation" ላይ አንድ ዙር ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለውጥ ለማምጣት የሥራ አመራሩ የለውጥ ቡድን አቋቁሞ እንቅስቃሴ ተጀምሯል::

- የመ/ቤቱ የአምስት አመት ረቂቅ ስትራቴጅክ እቅድ ተዘጋጅቶ በሥራ አመራር አካላት ግምገማ ተደርጎበት ጸድቋል።
- በፋይናንሻል ኦዲት፣ ክዋኔ ኦዲት እና በአስተዳደርና ፋይናንስ ላይ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ (BPR) ተጠናቆ ተግባራዊ እየተደረገ ከመሆኑም በላይ በውስጥ ኦዲት፣ በሥልጠናና የመረጃ አገልግሎት፣ በሕዝብ ግንኙነት እና በሕግ አገልግሎት ላይ የአሠራር ማሻሻያ ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ተግባር ለመቀየር በእንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን።
- የውጤት ተኮር የእቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ለመዘርጋት የጥናት ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በቀጣይ ሥልጠና ተሰጥቶ ወደ ተግባር ይሸጋገራል።
- የBPR ጥናት ተግባራዊ በመደረጉ የዘጠኙ ወራት የኦዲት አፈፃፀም ካለፉት ተመሳሳይ ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ጭማሪ አሳይቷል።
- በኦዲትና በሂሳብ አያያዝ ሙያ ለመሠማራት የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሚጠይቁ የተሟላ ማስረጃ ካቀረቡ ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥያቄያቸው ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል።
- በመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር PBS ተከታታይ ኦዲት ላይ ለተመደቡ ኦዲተሮች በተሰጠው ስልጠናና የቅርብ ክትትል መሠረት የኦዲቱ ጥራትና መጠን እየጨመረ መጥቷል።
- የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ (PBR) ጥናታቸው የተጠናቀቁትን ሥራዎች በመከለስ ማሻሻያ ለማድረግ እንዲረዳ በ BPR አሠራር ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል።
- በስትራቴጂክ እቅድና በአሰራር ማሻሻያ BPR ጥናት ውጤት መሠረት በመ/ቤቱ የሰው ኃይል ፍላጎት ላይ ያለውን ክፍተት በቅጥርና የደረጃ እድገት በመሙላት ላይ ይገኛል።
- የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲያገኙ የተደረገ ከመሆኑም በላይ የትምህርት ደረጃቸውን ከዲኘሎማ ወደ ዲግሪ እንዲያሳድጉ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ነው።
- በውጭ ኦዲት ኘሮጀክት አማካኝነት የተዘጋጁ የኦዲት ደረጃዎችና መመሪያዎች ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተርጉመው ለፌዴራልና ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ለማሰራጨት በዝግጅት ላይ ይገኛል ።

- በፌዴራልና በክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የጋራ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ 12ኛ የዋና ኦዲተሮች ጉባኤ ተካሂዷል፡፡
- የፋይናንሻል ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት የውጤት ተኮር ሥራ አፈጻጸም ሥርዓት በአፐኚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ ለሲ.ሰ.ማ.ን ስቴሪንግ ኮሚቴ ቀርቧል፡፡
- የመ/ቤቱን መዋቅር ለማስጠናት አስፈላጊውን የሥራ መዘርዝር (TOR) ተዘጋጅቷል፡፡
- የመ/ቤቱ የዌብሳይትና የኮምፒውተር መረብ (Network) የማጎልበት ሥራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡
- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በተመለከተ የመ/ቤቱ ሰራተኞች የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ትምህርት ሰጪ ፖስተሮችና ጽሁፎች የተሰራጩ ሲሆን በቀጣይም አስተማሪ የሆኑ ጽሁፎች ለስርጭት ተዘጋጅተዋል፡፡
- የመ/ቤቱ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ማስፈጸሚያ እቅድ ተዘጋጅቶ ለACE ኘሮጀክት የቀረበ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት ለተግባራዊነቱ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

- የመነሻ ጥናት (Baseline Survey) ለማከናወን መጠይቆች ተዘጋጀተዋል፡፡

የሚሉት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ሲሆኑ ዝርዝር አፈጻጸሙ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ በክፍል ሁለት ቀርቧል፡፡

## የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

15. በመ/ቤታችን በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተከናወኑ 160 ሂሳቦች ውስጥ 46 የፌዴራል እና 65 የክልል መ/ቤቶች በድምሩ 111 ሂሳቦች ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Except for Opinion)፣ 3 የፌዴራል እና 9 የክልል መ/ቤቶች በድምሩ 12 ሂሣቦች ጎላ ያለ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse Opinion)፣ በ4 የፌዴራልና በ10 የክልል መ/ቤቶች በድምሩ 14 ሂሣቦች ላይ ደግሞ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል የሚገልጽ አስተያየት (disclaimer of opinion) እንዲሁም በ2 የፌዴራል እና በ6 የክልል መ/ቤቶች በድምሩ 8

መ/ቤቶች አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean Opinion) የተሰጠባቸው ናቸው::

## በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

16. ምክር ቤቱ በዘመኑ ያጸደቀው በጀት ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ አጋዥ ሆኖ የሚያገለግለው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በጀቱ የተመደበላቸውን መ/ቤቶች የበጀት አፈፃፀም ኦዲት አድርጎ የሚያቀርበው የኦዲት ሪፖርት መሆኑ ይታወቃል:: በዚህም መሠረት የመንግሥት የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዲሞክራሲ ስርዓት የዳበረ ልምድ ባላቸው አገሮች እንደሚከናወነው ሁሉ በፌዴራል ዋና ኦዲተር በቀረቡት የገንዘብ አስተዳደርና የንብረት አጠባበቅ ድክመቶች የታየባቸውን መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ጠርቶ በመጠየቅና በድክመቶቹ ላይ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስዱ በማድረግ ተጠያቂነትን ለማጠናከር ለሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል::

 መ/ቤታችን በሚያካሂዳቸው ኦዲቶች በርካታ የሂሣብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የሚያጋጥሙ ቢሆንም፣ በዚህ ዘገባ የተካተቱት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሊደረጉ የሚገባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ሲሆኑ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

## የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

17. በ11 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 168,088.62፣ እና ከ5 የክልል መ/ቤቶች ብር 20,936.21 ጉድለት የተገኘ ሲሆን፣ በ4 የፌዴራል እና 4 የክልል መ/ቤቶች ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ማመዛዘን ሳይቻል ቀርቷል::

18. መ/ቤቶቹም የናዝሬት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ የንግድ ሥራ ኮሌጅ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት፣ የአፋር ክልል ውሃ ሀብት ቢሮ፣ የቃሉ ወረዳ ገንዘብና ኘላን ጽ/ቤት፣ የሚዛን ገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ማዕከል፣ የቀቢና ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ዋና ጽ/ቤት ናቸው:: ሂሳቡን ማመዛዘን ካልተቻለባቸው ዋና ዋና

ምክንያቶች ውስጥ የሂሣብ አመዘጋገብ ሥርዓቱ ለረዥም ጊዜ ሳይስተካከል መቆየቱ፣ የተሟላ የገንዘብ፣ የሰነድና የመዛግብት ርክክብ ባለመደረጉ፣ የሣጥን ከወጪ ቀሪ ሳይረጋገጥ የገንዘብ ያዥ ርክክብ በመፈፀሙ፣ የሚሉት ይገኙበታል።

ከነዚህ መ/ቤቶች ውስጥ የንግድ ሥራ ኮሌጅ እና የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአሠራር ግድፈቶችን እንደሚያስተካክሉ በላኩት መልስ ገልፀዋል።

## <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ</u>

19. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 38 እስከ 40 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ22 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 1.1 ሚሊዮን፣ በ28 የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች 61.5 ሚሊዮን በድምሩ 62.6 ሚሊዮን ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥ የደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ትምህርት ቢሮ ብር 28.5 ሚሊዮን፣ የአፋር ክልል ውሃ ሀብት ቢሮ ብር 16.2 ሚሊዮን፣ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ከተማ ልማት ቢሮ ብር 5.2 ሚሊዮን፣ የአፋር ክልል ማስታወቂያና የሕዝብ አደረጃጀት ቢሮ ብር 3.1 ሚሊዮን ጎላ ብለው የሚታዩ ናቸው። የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና የማስታወቂያ ሚኒስቴር በሰጡት መልስ በውዝፍነት የተገኘው የሰነድ ሂሳብ እንዲወራረድ ማድረጋቸውን በላኩት መልስ ገልጸዋል።

ይህ ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ በመ/ቤቶች የሥራ ማስኬጃ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የሥራ እንቅስቃሴ የሚያዳክም ከመሆኑም በላይ ለምዝበራና ብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶች የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው እንዲሰሩ አሳስበናል።

## <u>የገቢ ሂሣብ</u>

የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

## በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት

## ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ

20. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በፌዴራል መንግሥት 11 መ/ቤቶች ብር 1,729,002.75 በክልል መንግሥታት 33 መ/ቤቶች ብር 86,916.45 በድምሩ 1,815,919.20 ተገኝቷል፡፡

21. ገቢው ያልተሰበሰበበት ምክንያት ሲጣራ ለዕቃዎች የተተመነውን ታሪፍ አሳንሶ በመያዝ፣ የቀረጥ ነፃ መብት የሌላቸው ድርጅቶች ወይም ሰዎች ቀረጥ ሳይከፍሉ ዕቃ በማስገባታቸው፣ በኢንቮይስ ላይ ከተመለከተው የገቢ ዕቃ ብዛት በላይ በትርፍ ገቢ የሆኑ ዕቃዎች ላይ ቀረጥ እንዲከፈል ባለመደረጉ፣ እንዲሁም መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸውን የተከፋይ ሂሳብ ገቢ ግብር (withholding tax) ሳይቀንሱ በመቅረታቸው ያልተሰበሰበ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ

## አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

22. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን

## የታዩ የአሰራር ድክመቶች

23. በባለሥልጣን መ/ቤቱ እና በሥሩ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ጎላ ጎላ ያሉ ድክመቶች ተገኝተዋል፡፡

- በአዲስ አበባ ዓቢይ ቅርንጫፍ ለናሙና ከተመረጡ ቫውቸሮች ውስጥ ብር 6.2 ሚሊዮን የተሰበሰበባቸው 43 የገንዘብ መቀበያ ኮፒ ደረሰኞች በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ተያይዘው አለመገኘታቸው፣
- አዲት በተደረጉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብር ከፋዮች ከግብር መክፈያ የጊዜ ገደብ በኋላ ገቢ ሲያደርጉ በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ መሠረት ቅጣት የማይጣልባቸው መሆኑ፣
- የደቡብ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ የአጣሪ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ሳይቀርብ ብር 725.5 ሺህ ቅጣት እንዲነሳ ማድረጋቸው፣
- በተጨማሪ እሴት ታክስ መምሪያ የሂሳብ ሰራተኞች የገንዘብ መሰብሰብ ተግባር የሚያከናውኑ መሆኑ፣
- በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ሥር ባሉ ሶስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተሰብስቦ የተገኘ ብር 69.1 ሚሊዮን የግብር ከፋዮች አስፈላጊ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በደቡብ አብይ ቅ/ጽ/ቤት ከተመዘገቡ ሰባት የተለያዩ ድርጅቶች ብር 54.8 ሚሊዮን በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ መገኘቱ፣

የሚሉት ጎላ ያሉት የአሰራር ድክመቶች ናቸው::

በመሆኑም የታዩት የአሰራር ድክመቶች እንዲስተካከሉ እና ዘግይተው ግብር ገቢ በሚያደርጉት ላይ በደንቡ መሠረት አሠራሩ ተግባራዊ እንዲደረግ ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በላክነው የማሻሻያ ሀሳብና ለዋናው መ/ቤት በላክነው የተጠቃለለ ሪፖርት ገልጸናል::

## <u>በጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት እና ቅርንጫፎች የታዩ ልዩ ልዩ የአሰራር ድክመቶች</u>

24. በባለስልጣን መ/ቤቱ እና በስሩ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ጎላ ጎላ ያሉ ድክመቶች ተገኝተዋል::

- በጉምሩክ ባለሥልጣን የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 159.7 ሚሊዮን የያዙ

ዲክለራሲዮኖች እንዲሁም በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ 104 ዲክለራሲዮኖች ለኦዲት ያልቀረቡ ስለሆነ በእነዚህ ዲክለራሲዮኖች የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዲስ አበባ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 4.9 ሚሊዮን የሚያወጡ ዕቃዎች ባልተሟላ ማስረጃ የቀረጥና ታክስ ውሳኔ በመከናወኑ የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

- ከኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የጥራት ማረጋገጫ ሳይቀርብ በላጋር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋቸው ብር 6 ሚሊዮን የሆኑ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፣

- በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ የዕቃ ማጓጓዣ ዋጋ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ሳይካተት ብር 5.1 ሚሊዮን ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበ ሲሆን የዕቃ ማጓጓዣ ዋጋው በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ የዕቃው ዋጋ ዝቅ እንዲል በማድረጉ በዚሁ መሠረት ተሰልቶ ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ሳይሰሰበሰብ መቅረቱን፣
- በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ የኢንቮይስ ዋጋው ብር 634 ሺህ የሆነ 642 በርሜል ዘይት አካላዊ የዕቃ ፍተሻ (Physical inspection) ሳይከናወንበት እንዲለቀቅ መደረጉ፣

ታውቋል፡፡

ስለሆነም ያልተሰበሰበው የመንግሥት ገቢ እንዲሰበሰብና ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የአፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ እና ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲሆኑ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## <u>የወጪ ሂሣብ</u>

25. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሳቡም መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

## ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

26. በ17 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 2.92 ሚሊዮን ምንም ዓይነት ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ በደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ብር 1.3 ሚሊዮን፣ ጎላ ብሎ የተገኘ ነው::

27. ለሂሣቡ ደጋፊ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ካልቻሉ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም ተመሣሣይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል::

## የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

28. በ18 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 12.5 ሚሊዮን እንዲሁም በ42 የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች ብር 34.7 ሚሊዮን በድምሩ ብር 47.2 ሚሊዮን የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የአቅም ግንባታ ሚ/ር ብር 2.1 ሚሊዮን፣ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ብር 1.9 ሚሊዮን፣ የአማራ ክልል ውሃ ሀብት ልማት ቢሮ ብር 16.7 ሚሊዮን፣ የደቡብ/ሕ/ብ/ብ/ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ ብር 10.5 ሚሊዮን ጎላ ብለው የተገኙ ናቸው:: ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል::

## ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

29. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ17 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 165 ሺህ በ34 የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች ብር 130 ሺህ በድምሩ ብር 295 ሺህ ደንብና መመሪያ ሳይከተል ተከፍሎ ተገኝቷል:: ከዚህ ውስጥ ከመንግሥት ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ውጪ የተከፈለ እና በብልጫ የተከፈለ ደመወዝ የሚገኝበት ሲሆን ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል::

## ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

30. የግዢ ደንብና መመሪያ ሳይከበር፤ በ20 የፌዴራል መ/ቤቶች የብር 24.8 ሚሊዮን እንዲሁም በ53 የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች የብር 30 ሚሊዮን በድምሩ የብር 54.8 ሚሊዮን ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ጎላ ያለው የአፋር ክልል የውሃ ሃብት ቢሮ ለውሃ ግንባታ ዕቃዎች ግዥ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ በብር 20.2 ሚሊዮን እንዲሁም በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በብር 11.1 ሚሊዮን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በብር 6.3 ሚሊዮን፣ የተፈጸሙ ግዥዎች ጎላ ብለው የተገኙ ናቸው፡፡

31. በሪፖርታችን በሰጠነው ማሳሰቢያ መሠረት 4 የፌዴራል መ/ቤቶች ለወደፊቱ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው እንደሚሰሩ እና የሐረር ፖሊስ ሆስፒታል ደግሞ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱን ገልጿል፡፡

የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ የዕቃ ግዢ መፈጸም ተገቢ ላልሆነ ወጪ፣ ለምዝበራ፣ ለጥፋትና ጉድለት የሚዳርግ በመሆኑ የመንግሥትን የዕቃ ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

## የወጪውን ትክክለኛት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ

32. ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ተከትለው መፈጸማቸውን ለማጣራት ተሞክሮ በ3 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ብር 6.7 ሚሊዮን እና በ4 የክልል መ/ቤቶች ብር 1.5 ሚሊዮን በድምሩ ብር 8.2 ሚሊዮን ተገቢ የሆኑ ማስረጃዎች ተሟልተው ባለመገኘታቸው ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ብር 1.7 ሚሊዮን እና የባለሥልጣኑ የውጭ መረጃ ዋና መምሪያ ብር 4.8 ሚሊዮን፣ እንዲሁም የደሴ ዙሪያ ወረዳ ገንዘብና ኘላን ጽ/ቤት ብር 1.1 ሚሊዮን ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ለወደፊቱ ማስረጃዎች ተሟልተው መያዝ እንዳለባቸው እና ያልተገኙትም ማስረጃዎች እንዲሟሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት

33. የተገዛው ዕቃ ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት መፈጸሙ ሲጣራ፣ በ13 የፌዴራል መ/ቤቶች በብር 14.5 ሚሊዮን ለተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ ታውቋል፡፡ ከነዚህ መ/ቤቶች መካከል የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሰጠው መልስ ለእቃዎቹ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካለመቆረጡ በስተቀር ንብረቱ ገቢ መሆኑን ገልጿል፡፡

## የዕቃና ንብረት አስተዳደር

34. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ12 የፌዴራል መ/ቤቶች እና በ23 የክልል መንግሥት መ/ቤቶች በድምሩ በ35 መ/ቤቶች፣ የአላቂና ቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ባለመቋቋሙ፣ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው በመሆኑ፣ የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይደረግ በመሆኑ፣ ቆጠራ ቢደረግም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር በመሆኑ እና በአንዳንድ መ/ቤቶች ደግሞ ተጀምሮ የነበረው አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ በመቋረጡ ምክንያት የንብረት ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የተጠቀሱትን የአሠራር ስህተቶች በማረም ለወደፊቱ በመንግሥት የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ መመሪያ መሠረት እንዲሰሩ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## ተሽከርካሪ

35. የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ በ10 የፌዴራል መ/ቤቶች እና በ16 የክልል መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- በሶስት የፌዴራል መ/ቤቶች 15 ተሽከርካሪዎች እና በአራት ክልል መንግሥታት 55 በድምሩ 70 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ

ያልቀረበላቸው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር 9፣ በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን 15፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መ ትምህርት ቢሮ 10 ተሽከርካሪዎች ጎላ ያሉ ናቸው::

- በ4 የፌዴራል እና በ5 የክልል መ/ቤቶች በድምሩ 284 ተሽከርካሪ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በግብርና ሚኒስቴር 119፣ በውሃ ሀብት ሚኒስቴር 48 እና በሐረሪ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ 16 ተሽከርካሪዎች ጎላ ያሉት ናቸው::
- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር 16 ተሽከርካሪዎች እና በውጭ ጉዳዩ ሚኒስቴር አንድ ተሽከርካሪ በድምሩ 17 ተሽከርካሪዎች አካል ላይ የተገኘው የሻንሲና የሞተር ቁጥር በባለቤትነት መታወቂያ ላይ ከተመለከተው ቁጥር ጋር ልዩነት መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ የሰሌዳ ቁጥሩ፣ ሊብሬ፣ የሞተር ቁጥሩና ሻንሲ ቁጥሩ የማይታወቅ 1 ተሽከርካሪ ተገኝቷል::

የባለቤትነት መታወቂያ የሌላቸውም ሆነ በሻንሲና ሞተር ቁጥራቸው ላይ ልዩነት የተገኘባቸው ተሽከርካሪዎች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ መኪናዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ እንዲደረግ አሳስበናል /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በልዩ ጥራዝ ቁጥር 2 ተመልክቷል/::

## የበጀት አጠቃቀም

36. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ12 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 39.5 ሚሊዮን በ33 የክልል መ/ቤቶች ብር 7.6 ሚሊዮን በድምሩ ብር 47.1 ሚሊዮን በዋና ዋና የወጪ መደቦች በደንቡ መሠረት ዝውውር ሳያስፈቅዱ ከበጀት በላይ ወጪ አድርገው ተገኝተዋል:: ከዚህ ውስጥ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ብር 17.5 ሚሊዮን፣ የደህንነት የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ብር 14.7 ሚሊዮን፣ የድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ብር 2.7 ሚሊዮን እና የአፋር ክልል ውሃ ሀብት ቢሮ ብር 1.8 ሚሊዮን ጎላ ያሉት ናቸው:: በሌላም በኩል በ38 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 141.3 ሚሊዮን፣ በ60 የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች ብር 48.8 ሚሊዮን ለዋና ዋና የወጪ ሂሳብ መደቦች

ከተደለደለው በጀት ውስጥ በድምሩ ብር 190.1 ሚሊዮን ስራ ላይ ሳያውሉት ተገኝተዋል፡፡ ያልተሰራበት በጀት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 27.6 ሚሊዮን፣ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ብር 14.9 ሚሊዮን፣ እና የአማራ ክልል ውሃ ሀብት ልማት ቢሮ ብር 9.6 ሚሊዮን ኀላ ያሉት ናቸው፡፡

## ባለፉት አመታት በላክናቸው ኦዲት ሪፖርቶች መሠረት

## እርምጃ ያልወሰዱ መ/ቤቶች

37. ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ በቀድሞው የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን እና በግብርና ሚ/ር ባለፈው በጀት ዓመት በተሰጡት የኦዲት ሪፖርት ውጤትና የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት በተሟላ መልኩ እርምጃ ያልወሰዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

    በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ አለመውሰድ አግባብ አለመሆኑን ገልጸን የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን በቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ አስገንዝበናል፡፡

## የፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ግኝትና አስተያየት

38. የ1996 በጀት ዓመት አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

    - በ1996 በጀት ዓመት ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተላለፈው የድጋፍና ልዩ ድጎማ በጀት ሥራ ላይ የዋለበትን ሁኔታ የሚገልጽ የሂሳብ ሪፖርት ሳይቀርብ ወደ ክልሎች የተላለፈው ገንዘብ በቀጥታ ሥራ ላይ እንደዋለ ተደርጎ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

      የቀረበውም የሂሣብ መግለጫ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 መሠረት የክልል መንግሥታት እና የከተማ መስተዳድሮች የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ በሚያሳይ መልኩ አልተዘጋጀም፡፡

ይህንን አስመልክቶ የመጨረሻ እልባት ለመስጠት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለክልሎች የተላለፈው በጀት ሥራ ላይ እንደዋለ ተቆጥሮ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበት እና በሂሣብ መግለጫው ውስጥ መካተት ያለበት ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለው ትክክለኛው ወጪ መሆን እንደሚገባው ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን፣ ሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ በወጪ የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚያጠና ከሁለቱ መ/ቤቶች የተወጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብ እና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/84 ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1987 አስቀድሞ ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ እና የዘቀጠ ትርፍ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

  ይሁን እንጂ በነዚህ አዋጆች መሠረት ከእያንዳንዱ ድርጅት ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ተሞክሮ የውዝፍ ዕዳ መከታተያ ሌጀሮችና ማስረጃዎች ለኦዲት በሚያመች መልኩ ተሟልተው ባለመቅረባቸው ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰቡን ማጣራት አልተቻለም፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰጠው መልስ የማስተካከያ እርምጃ ተደርጎ አዲስ ሌጀር ተከፍቶ ሥራዎቹ እንዲስተካከሉ መደረጉንና ውዝፍ የዋና ገንዘብና የዘቀጠ ትርፍን በተመለከተ ደግሞ ከመዝገብ ለመሰረዝ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ስለተጠናቀቀ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለመንግሥት ቀርቦ እንደሚሰረዝ ገልጿል፡፡

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይታወጅ የተለያዩ ባለበጀት መ/ቤቶች በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች ብር 163.56 ሚሊዮን ከተደለደለው በጀት በላይ ተጠቅመው ተገኝተዋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ ባለበጀት መ/ቤቶች ያቀረቡትን የበጀት አጠቃቀም ዘገባ ለኦዲት

ከማቅረብ በስተቀር በመ/ቤቶቹ ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑንና ለወደፊቱ የበጀት አፈፃፀምን ለማሻሻል የሚረዳ የበጀት ዝውውር መመሪያ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተጠቅሷል፡፡ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ ተከትለው በማይሰሩ መ/ቤቶች ላይ የመንግሥት የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጠንከር ያለ ክትትል በማድረግ በዚህ ረገድ እየታየ ያለው የበጀት አፈፃፀም ችግር የሚታረምበትን መንገድ መቀየስ አስፈላጊ መሆኑን እናሳስባለን፡፡

- በገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 25(3) መሠረት መንግሥት ከአገር ውስጥ ሊበደር የሚገባው የግምጃ ቤት ሰነድ ባለፉት ተከታታይ በጀት ዓመታት ውስጥ በተሰበሰበው አማካይ የመደበኛ ገቢ ከሀያ አምስት (25%) በመቶ መብለጥ እንደሌለበት የተደነገገ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ውስጥ መንግሥት መበደር ከሚገባው በላይ ብር 1,245.4 ሚሊዮን ከግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ባለበጀት መ/ቤቶች በቻናል 2 ያገኙትን እርዳታ በመንግሥት የሂሳብ መግለጫ ውስጥ ለማካተት እንዲረዳ የሂሳብ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ልማት ሚ/ር በእያንዳንዱ በጀት ዓመት መጨረሻ በደብዳቤ ጥያቄ በማቅረብ ምላሽ የሰጡትን መ/ቤቶች ሂሳብ በመመዝገብ ላይ እንዳለ የሚታወቅ ቢሆንም፣ ባለበጀት መ/ቤቶች ያገኙትን እርዳታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁ ቢቀሩ ሪፖርት ያላደረጉትን መ/ቤቶች ለማወቅና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ በቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የእርዳታ ገቢ ሂሳብ መንግሥት በበጀት ዓመቱ ያገኘው ዕርዳታ ይህ ብቻ ነው ብሎ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡ ለወደፊቱ አሰራሩን ለማሻሻል ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መመሪያ መተላለፉን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከተገለፁት ልዩ ልዩ የአሰራር ግድፈቶች በስተቀር በእኛ አስተያየት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የዘመኑን የመንግሥት ሂሣብና የፋይናንስ አፈፃፀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያል፡፡

## የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን

## የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

39. የኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት፤ በአጥጋቢ ሁኔታ እየተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ኃላፊነቱን በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተወጣ ደግሞ ምክንያቶችን ለይቶ በማውጣት ለሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሣብ ለመስጠት ነው፡፡

40. ኦዲቱ ያተኮረው ብሔራዊ የተስማሚነት ምዘና ሥርዓት መቋቋሙንና በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፡፡ በዚሁ የምዘና ሥርዓት መሠረት የላብራቶር ፍተሻና የካሊብሬሽን አገልግሎት አሰጣጥ አጥጋቢ መሆኑን ማጣራት እና፣ የምርትና የመለኪያ መሣሪያዎች የቴክኒክ ደንቦችን የማስፈፀም ሥራ እንዲሁም ምርቶችና የሲስተም ሠርተፊኬሽን አገልግሎት አሠጣጥ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡ በኦዲቱ የታዩ ልዩ ልዩ የአሰራር ድክመቶች፣ በባለሥልጣኑ የተሰጡ ማብራሪያዎችና የማሻሻያ ሃሳቦች በልዩ ጥራዝ የቀረበ ሲሆን፣ ጎላ ጎላ ያሉት ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- የባለሥልጣን መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 102/1990 ሥልጣን የተሰጠው ቢሆንም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ወቅት ሥርዓቱ ያለመዘርጋቱ፣
- በግብርና፣ በኢንዱስትሪው፣ በጤና፣ በምርምር ተቋማት እና እንዲሁም በገበያ ሥርዓት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የተለያዩ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ብሔራዊ የሜትሮሎጂ /መለኪያ/ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ በተለያዩ ተቋማት ያሉ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የምርት ሰርቲፊኬሽን፣ የኢንስፔክሽን እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ያልተጀመረ በመሆኑ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ አገር የሚልኩ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ደረጃ ለማሰጠት የምርት ናሙና ወደ ውጪ አገር ለመላክ መገደዳቸውንና ይህም ለተጨማሪ ወጪ እና የጊዜ ብክነት የዳረገ መሆኑ፣

- ምርቶች ወይም የምርት ሂደቶች አግባብ ካላቸው አስገዳጅ የሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር ተስማሚ ሆነው ካልተገኙ ባለስልጣን መ/ቤቱ እርምጃ ለመውሰድ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ተስማሚ ያልሆኑ ምርቶች ወይም የምርት ሂደቶች ሲያጋጥሙ ድርጅቶቹ ሥራ እንዲያቋርጡ በጽሑፍ የሚያስታውቅ ቢሆንም፣ ባለሥልጣኑ በፃፈው ደብዳቤ መሠረት ውሳኔው ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- አስገዳጅ የሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች (የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ፈቃድ ሣይሰጣቸው መመረት የሌለባቸው) ያላቸውን ምርቶች የሚያመርቱ ወይም የምርት ሂደቶችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች የሥራ እንቅስቃሴ ከመጀመራቸው በፊት ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው በህግ የተደነገገ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት መረጃ በተሰበሰበባቸው በአዲስ አበባ መስተዳድር፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በአፋር፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች፣ በሐረሪ እና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የብሎኬት፣ የምግብ ዘይት፣ የምግብ ጨው፣ ሳሙና፣ ኘላስቲክና የኘላስቲክ ውጤቶችን ለማምረት ፈቃድ ካወጡ 593 ድርጅቶች ውስጥ 62 ድርጅቶች (11%) ብቻ የባለስልጣኑ የጥራት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የተሰጣቸው መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚዛንና የመስፈሪያ መሣሪያዎችን የሚያመርቱ፣ ከውጪ የሚያስመጡና የሚያከፋፍሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ዝርዝር መረጃ መያዝ ያለበት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ድርጅቶች ያመረቱትንና ያከፋፈሉትን ሚዛንና የመስፈሪያ መሣሪያዎች በየሶስት ወሩ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው በሚዛንና መስፈሪያ ደንብ ቁጥር 431/1965 የተደነገገ ቢሆንም ይህ ተግባር በደንቡ መሠረት ያለመፈጸሙ ተረጋግጧል:: ይህም ትክክለኛ ያልሆኑ የሚዛንና የመሥፈሪያ መሣሪያዎች ለንግድ ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፣
- ተንቀሳቃሽ የሆኑ የፈሳሽ ማጓጓዣ መሣሪያዎች፣ ተሽጋጋሪ ሚዛኖች (weight bridges)፣ ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ የነዳጅ ማደያዎች እና የነዳጅ መለኪያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊትም ሆነ አገልግሎት ላይ እያሉ ትክክለኛነታቸው በባለሥልጣኑ መረጋገጥ ያለበት ቢሆንም ይህ

የሚከናወነው ባለንብረቶች በራሳቸው ፈቃድ መሣሪያዎቻቸው እንዲመረመሩላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ ነው። ይህም በመሣሪያዎቹ ተገልጋይ የሆኑ ድርጅቶችና ሕብረተሰቡ ትክክለኛ አገልግሎት እንዳያገኙ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የጥራትና የደረጃዎች ደንቦችን ለማስፈጸም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት የቡናና የሻይ ደረጃ ቁጥጥር ለቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር፣ የቆዳና ሌጦን ደረጃ ቁጥጥር ለቀድሞው የከብትና የሥጋ ቦርድ ውክልና የተሰጠ ቢሆንም መ/ቤቶቹ በደረጃዎቹ መሠረት ስለመስራታቸው ክትትል የማያደርግ ከመሆኑም በላይ አስገዳጅ የሆኑ ደረጃዎች የሚመለከታቸው ምርቶች በብዛት ከሚመረትባቸው ከአዲስ አበባ መስተዳድር፣ ከትግራይ ክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ንግድ ኢንዱስትሪ ቱሪዝም ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና ከአፋር ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር ቅንጅታዊ አሠራር የሌለው መሆኑ፣

- የጥራትና የደረጃዎች ደንቦችን ለማስፈጸም ከጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በ1996 በጀት ዓመት በጉምሩክ መ/ቤት ላይ በተደረገው የፋይናንሻል ኦዲት እንደተረጋገጠው ዋጋቸው ብር 1.3 ሚሊዮን እና በ1998 ደግሞ ብር 6 ሚሊዮን የሆኑ እቃዎች የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ማረጋገጫ ሳይቀርብ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል።

41. ከላይ የተመለከቱትን የአሰራር ችግሮች በተመለከተ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በፋይናንስና በሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 መሠረት በየክልሉ ያሉ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሰጪ አካላት ለባለሥልጣኑ ተገቢውን ትብብር ባለማድረጋቸው፣ አንዳንድ አሰራሮችን ለማሻሻል ረቂቅ ደንቦችና መመሪያዎች የተዘጋጁ ቢሆንም በወቅቱ ባለመጽደቃቸው፣ የክልል ንግድ ቢሮዎች የሚዛንና የመሥፈሪያ መሳሪያዎች አስመጪ፣ አምራችና አከፋፋዮችን ለይተው ባለመያዛቸው በደንብ ቁጥር 431/19965 መሠረት ኃላፊነቱን መወጣት አለመቻሉን ገልጸዋል።

42. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተገቢው ክትትል ተደርጎ እንዲጸድቁ ማድረግ ያለበት ሲሆን በአሰራር ረገድ የታዩትን ድክመቶች በማሻሻል ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ጥረት ማድረግ እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል።

## የትራንስፖርት ባለሥልጣን የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

43. የኦዲቱ ዓላማ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ትራስፖርት እና የመንገድ ደህንነትን በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ኢኮኖሚያዊ፣ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ኃላፊነቱን በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተወጣ ደግሞ ምክንያቶችን ለይቶ በማውጣት ለሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው።

44. በኦዲቱ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ድክመቶች፣ በባለሥልጣኑ የተሰጡ ማብራሪያዎችና የማሻሻያ ሀሳቦች በልዩ ጥራዝ የቀረበ ሲሆን ጎላ ጎላ ያሉት ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

- ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት አደጋ የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲኖራቸው እና በህዝብ ማመላለሻ ለሚጓጓዙ መንገደኞችና ዕቃዎች ሊኖር ስለሚገባው የመድን ዋስትና ሽፋን ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ በማውጣት ስራ ላይ መዋሉን መከታተል ለባለስልጣኑ የተሰጠ ኃላፊነት ቢሆንም መመሪያው ያልወጣ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የመንገድ ሁኔታና በአሁኑ ወቅት ያለውን የተሽከርካሪዎች ብዛትና የቴክኖሎጂ እድገት ያገናዘበ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ፣ የባለሞተር ተሽከርካሪ ፍጥነት ወሰን እና የአገር አቋራጭ ንግድ ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ብቃት ምዝገባ ደንብ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል የሚጠበቅበት ቢሆንም አሁን እየተሠራበት የሚገኘው ደንብ በ1961 እና በ1956 ዓ.ም. የወጣ በመሆኑ፣
- የባለሞተር ተሽከርካሪና ተሣቢ ክብደትና መጠን ደንብ፣ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ እና በእርጅናና በቴክኒክ ብቃት አለመሟላት አደጋ ከማድረሳቸው በፊት መወገድ ስላለባቸው ተሽከርካሪዎች መመሪያ፣ የአካባቢ መበከልን ለመከላከል ከተሽከርካሪዎች ስለሚወጣው ጪስ እና የጋዝ መጠን እንዲሁም

የተሽከርካሪዎችን አካል ለውጥ ተከትሎ የሚወጣውን አግባብ ያልሆነ የወንበር ቁጥር መጨመር መከላከል የሚያስችል መስፈርት ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ማዋል የሚኖርበት ቢሆንም፣ አዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ደንቡ ያልተዘጋጀና ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

- የአገር አቋራጭ ንግድ ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ብቃት ምዝገባ ደንብ አዘጋጅቶ ስራ ላይ ማዋል ያለበት ቢሆንም አሁን እየተሠራበት የሚገኘው ደንብ በ1961 ዓ.ም. የወጣ ሲሆን ይህም በአሁኑ ወቅት ያለውን ያገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል አለመደረጉ፣
- የባለሞተር ተሽከርካሪ እና ተሣቢ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ደንብ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል የነበረበት ቢሆንም ይህ ደንብ በ1961 ወጥቶ በ1975 እና በ1993 የተሻሻለ ቢሆንም በአግባቡ በሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- በፌዴራል እና በክልሎች የሚተዳደሩ መንገዶች አስፈላጊው የመንገድ ላይ የትራፊክ ምልክቶች ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን፣ ከጅማ-ቦንጋ-ሚዛን ተፈሪ - ማሻ ጐሬ ባሉት መንገዶች ላይ ተገቢው የትራፊክ ምልክቶች ያልተሟላቸው መሆኑ፣
- የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን አስመልክቶ በብሔራዊ ደረጃ እና በክልሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት የሚያስተባብርና የሚመራ አካል በህግ ሊቋቋም የሚገባ ቢሆንም የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት ራሱን ችሎ በአዋጅ ባለመቋቋሙ ከጽ/ቤቱ የሚጠበቁት ሥራዎች ከሌሎች የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሥራዎች ጋር በተደራቢነት የሚከናወኑ በመሆኑ በአሠራር ላይ የሥራ መጓተትን እንዲሁም የጽ/ቤቱ ሠራተኞች በጊዜያዊነት የሚቀጠሩ በመሆናቸው የሠራተኞች በየጊዜው ከሥራ መልቀቅን ያስከተለ መሆኑ፣
- በፌዴራልና በክልሎች የመንጃ ፈቃድ በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት ለሥልጠና የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሊሟሉ የሚገባ ቢሆንም በከፋ ዞን፣ ሸካ ዞን፣ ጅማ ዞን፣ ጅማ ከተማ መስተዳድር፣ ቤንች ማጂ ዞን፣ ጉራጌ ዞን፣ ከንባታ ጠንባሮ፣ ወላይታ፣ ስልጤ፣ ሐረርጌና ጅጅጋ ዞኖች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በበቂ ሁኔታ አለመሟላታቸው፣

- በክልሎችና ዞኖች በሁሉም ደረጃ የሚመደቡ አሠልጣኞች በሥልጠና መስፈርቱ መሠረት ለየደረጃው የተመደበውን የሞያ መስፈርት የሚያሟሉ መሆን ያለባቸው ቢሆንም በጉራጌ ዞን፣ ሀድያ፣ ስልጤ፣ ወላይታ፣ ከንባታ ጠንባሮ፣ ባሌ፣ አርሲ፣ ጅማ፣ ቦረና፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ኢሊባቡር፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ እና ቤንች ማጅ ዞን ያሉ አሠልጣኞች ተፈላጊውን የችሎታ መስፈርት አለማሟላታቸው፣ በአብዛኞቹ ዞንና ክልሎች በሁሉም ደረጃ ለሚሰጡ የመንጃ ፈቃዶች የማለማመጃ ተሽከርካሪ ችግር ያለባቸው መሆኑ እና የተለያዩ የተሽከርካሪ ክፍሎችን የያዘ የማስተማሪያ ክፍሎች ያልተሟሉ መሆኑ፣
- የመንጃ ፈቃድ በአንድ ዞን ወስደው በድጋሚ በሌላ ዞን ለመውሠድ የሚሞክሩ ህገወጦችን ለመቆጣጠር በሁሉም ክልሎችና ዞኖች ወጥነት ያለው አሠራር መዘርጋት ያለበት ቢሆንም በኦሮሚያ ክልል ጅማ ከተማ መስተዳድር፣ ጅማ ዞን፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ አርሲ ዞን፣ ቦረና ዞን፣ ምስራቅ ወለጋ፣ አለምገና፣ ባሌ ዞን፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ ሸዋ እንዲሁም በትግራይ ክልል ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የተጠናከረ አሠራር የሌለ ከመሆኑም በላይ አስመስሎ መስራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል በሁሉም ክልሎች አንድ ወጥ የሆነ የመንጃ ፈቃድ ደብተሮች ህትመት የሌለ መሆኑ፣
- በሀገር ውስጥ ለሚገጣጠሙና ለሚቀጠቀጡ ተሽከርካሪዎች አካል አሠራር ዲዛይን፣ ስታንዳርድና መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም 25 ሠዎችን ለሚይዙ ተሽከርካሪዎች አካል አሠራር ዲዛይን፣ ስታንዳርድና የአፈፃፀም ቼክ ሊስት አለመዘጋጀቱ፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

45. ከላይ የተመለከቱትን የአሰራር ችግሮች በተመለከተ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሶስተኛ ወገን ለሚያደርሱት አደጋ የመድን ዋስትና መመሪያ እና የፍጥነት መቆጣጠሪያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለትራንስፖርትና መገናኛ የቀረበ ቢሆንም ያለመጽደቁን፣ የባለሞተር ተሽከርካሪና ተሳቢ ክብደትና መጠን ደንብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያልተደረገው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ይህንን የተመለከተ ጥናት

ባለማቅረቡ፣ በ1961 የወጣው የአገር አቋራጭ የንግድ ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ብቃት ምዝገባ ደንብ ተሻሽሎ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢቀርብም እንዳልጸደቀ፣ የብሔራዊ መንገድ ደህንነት ም/ቤት ጽ/ቤትን በህግ ለማቋቋም ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል መላኩን፣ ለሥልጠና የሚፈለጉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማሟላት ያለባቸው እራሳቸው ክልሎቹ ቢሆኑም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀለል ላሉ ኘሮጀክቶች ድጋፍ የሚያደርግ ቢሆንም ዞኖች ኘሮጀክት በመቅረጽ ረገድ ባለባቸው የሰው ኃይል ችግር ተጠቃሚ መሆን አለመቻላቸውን የሚሉት ከተሰጡት ማብራሪያዎች ጥቂቶቹ ሲሆኑ በልዩ ጥራዝ በቀረበው ሪፖርት ዝርዝር ሁኔታው እና መ/ቤታችን የሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

46. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልጉ ደንብና መመሪያዎች ጸድቀው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ሲሆን በሪፖርታችን የተመለከቱት ልዩ ልዩ የአሰራር ድክመቶች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ሊስተካከሉ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## በመ/ቤቱ የተከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራት

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የኦዲት ሥራ ተግባራት በተጨማሪ መ/ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ቀጥሎ የተመለከቱትን አከናውኗል፡፡

### ለኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ መስጠትና መከታተልን በተመለከተ

47. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/14 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ የሙያ ብቃትን ገምግሞ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ኮሚቴ ተቋቁሞ በ1998 በጀት ዓመት ለ46 የሂሳብ አዋቂዎችና ለ7 ኦዲተሮች በ1999 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ2 የግል ኦዲተሮችና 28 የግል ሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡

48. በተመሳሳይ ሁኔታ የውስጥ ኦዲትን ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ በተለይም በልማት ድርጅቶች በውስጥ ኦዲተርነት የሚመደቡ ሠራተኞች ከመመደባቸው በፊት የሙያ ብቃታቸውን በማጥናትና ደረጃ በማውጣት በ1998 በጀት

ዓመት አና ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ168 የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ማረጋገጫ እንዲሰጥ አድርጓል፡፡

49. ባለሙያዎቹ ሙያው በሚጠይቀው መሠረት ተግባራቸውን ማከናወናቸውንና ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን መ/ቤታችን አቅም በፈቀደ መጠን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ አንዳንድ የግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች ሙያው የሚጠይቀውን ደረጃ እና ሥነ ምግባር ጠብቀው የሚፈለገውን አገልግሎት በመስጠት ላይ አለመሆናቸውን መ/ቤታችን ሲያረጋግጥና ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ ቅሬታና ስሞታ ሲቀርብ ጉዳዩ በመ/ቤቱ በተቋቋመው ሀገር አቀፍ ሰርተፊኬሽን ኮሚቴ እየተጣራ ተገቢው የዲሲኘሊን እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በሶስት የግል ኦዲት ድርጅቶች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ተወስዷል፡፡

## የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴን አቅም በስልጠና መገንባት

በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቅርቡ የተቋቋመውን የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲረዳው በማሰብ የክልል መንግሥታት ም/ቤት የወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች እና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊዎች በተገኙበት ከውጭ ኦዲት ኘሮጀክትና የኦዲት ተቋማትን ለማጠናከር ከካናዳ መንግሥት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኦዲት ሪፖርት ምንነትንና በባለበጀት መ/ቤቶች የሚገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች፣ የወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተግባራትና ከዋናው ኦዲተር መ/ቤት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት የካናዳ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተሞክሮና የካናዳ የመንግሥት ሂሳብ ኮሚቴ (PAC) ልምዶች እንዲሁም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የሚሉትን ርዕሶች ያካተተ ስልጠና፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና ከመ/ቤታችን በተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ይህም ስልጠና ቋሚ ኮሚቴው በአስፈጻሚው አካል ላይ በሚያደርገው የበጀት አፈፃፀም እና ከመንግሥት ወጪ አስተዳደር ጋር የተያያዙ የአገሪቱ ሕጎች፣ ደንቦች፣ ኘሮግራሞችና ስትራቴጂዎችን በአግባቡ ተፈጻሚ

መሆናቸውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል፡፡

## መ/ቤቱን ለማጠናከር የተወሰዱ እርምጃዎች

50. መ/ቤቱን ለማጠናከር አንዳንድ እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የመ/ቤታችን እና የክልል ኦዲት ቢሮዎች ኦዲተሮችን ሙያ ለማሳደግ ከአየርላንድ መንግሥት በተገኘ ድጋፍ በርካታ ኦዲተሮች ለተመሠከረለት የሂሳብ አዋቂነት የሚያበቃ የተልዕኮ ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሠረት 7 የመ/ቤታችን ኦዲተሮች ፈተናውን በአጥጋቢ ሁኔታ አልፈው የተመሠከረላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሆኑ ሲሆን በመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሱና በቅርቡ ትምህርቱን ያጠናቅቃሉ ተብለው የሚጠበቁ 4 ሠራተኞችን ጨምሮ በድምሩ የተመሰከረላቸውን የሂሳብ አዋቂዎች ወደ 11 ከፍ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ 40 የክልል እና የፌዴራል ኦዲተሮች ትምህርቱን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

51. መልካም አስተዳደር፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው እንቅስቃሴ የኦዲት ተቋማት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ የካናዳ መንግሥት የኦዲት ተቋማትን ለማጠናከር ድጋፍ ለማድረግ በተስማማው መሠረት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን እና ሁለት የክልል መንግሥታት ኦዲት መ/ቤቶችን ያካተተ ኘሮጀክት ተቀርጾ ይፋ እንስቅቃሴ ከጀመረ ሶስት ዓመት ሆኖታል፡፡

በዚህ መሠረት ኘሮጀክቱ የሥልጠና፣ የኮምፒውተርና የተሽከርካሪ መኪና ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፣ የኦዲት ተቋማቱ የሚገለገሉበት የኦዲት መመሪያ ዓለምአቀፍ ደረጃ የጠበቀ እንዲሆን የሙያ ዕገዛ በማድረግ ላይ ነው፡፡

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ያጋጠሙ ችግሮች

52. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት እያደረገ ቢሆንም ገና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅበት ግልፅ ነው፡፡ ኃላፊነቱን በተሻለ ሁኔታ እንዳይወጣና ተግባሩን በተሟላ ሁኔታ እንዳያከናውን ካደረጉት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፡፡

## የሰው ኃይል እጥረት እና ፍልሰት

53. መ/ቤታችን በ1989 በፀደቀው አዲስ መዋቅር 462 ሠራተኞች እንዲኖሩት የተፈቀደ ቢሆንም 129 የሥራ መደቦች በባለሙያ እጥረት ምክንያት ለመሸፈን አልተቻለም፡፡ የሰው ኃይል እጥረት ዋናው ምክንያት በገበያ ላይ ተፈላጊውን ባለሙያ ለማግኘት አለመቻል ብቻ ሳይሆን ያሉትም ባለሙያዎች በመ/ቤታችን ጠቃሚ ልምድ ካካበቱ በኋላ መ/ቤቱን ለቀው በውጪ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ተቋማት በከፍተኛ ደመወዝ ሊቀጠሩ መቻላቸው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በ1999 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 17 ባለሙያዎች መ/ቤቱን ለቀው ሄደዋል፡፡

54. ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ እንዲቻል መ/ቤታችን አዲስ የደመወዝ ስኬል አጥንቶ እንዲፈቀድ ያቀረበው ጥያቄ በምክር ቤቱም በመደገፉ ከጥር/1995 ጀምሮ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ሊፈቀድለት ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተፈቀደው ስኬል በመ/ቤታችን ተጠይቆ በምክር ቤቱ የተደገፈውን ያልተከተለ እና የሥራ መደብን ሳይሆን የትምህርት ደረጃ መሠረት ያደረገ በመሆኑ እና ከተፈቀደም ከአራት ዓመት በላይ ስለሆነው ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በየጊዜው ያሳሰብን ቢሆንም እስካሁን መፍትሔ አላገኘም፡፡ በመሆኑም የደመወዝ እስኬሉ እንዲስተካከል ም/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ እናሳስባለን፡፡

## የመዘዋወሪያ አበል ችግር

55. የመ/ቤቱ የሥራ ፀባይ ከከተማው ዳር እስከዳር በሚገኙ መ/ቤቶች ተዛውሮ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት ዘገባችን በተደጋጋሚ እንደገለጽነው፣ ከታህሣሥ 1 ቀን 1970 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያለው የመዘዋወሪያ አበል በወቅቱ በነበረው የነዳጅ ዋጋ ተሰልቶ ሲሆን፣ አሁን ከ29 ዓመታት በኋላ የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ምክንያት የታክሲ መጓጓዣ ዋጋ የጨመረ በመሆኑ፣ ከከተማው በየጊዜው መስፋፋትና የመ/ቤቶች በተራራቀ ቦታ መገኘት ጋር ተዳምሮ ኦዲተሮቻችንን ከመ/ቤት ወደ መ/ቤት አዘዋውሮ ማሠራት አዳጋች ሆኗል፡፡

56. ይህንኑ ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ የመዘዋወሪያ አበል ማሻሻያ እንዲደረግ ከ6 ዓመታት በፊት ጥያቄ የቀረበና ከዚያም ወዲህ በየጊዜው ጥያቄ በማቅረብ ላይ ብንሆንም የሥራ ጸባያቸው ከቦታ ቦታ መዘዋወርን

ከማይጠይቅ መ/ቤቶች ጋር በአጠቃላይ ይታያል በሚል ባለመደገፉ የሠራተኛውን ሞራል በከፍተኛ ደረጃ የጎዳው መሆኑንና ሥራን በሰዓቱ ገብቶ ለማከናወን አዳጋች እየሆነ መምጣቱን ምክር ቤቱ ሊያውቀው ይገባል፡፡ ስለሆነም፤ መ/ቤታችን ደጋግሞ በጠየቀው መሠረት የመ/ቤታችንን የተለየ የሥራ ባሕርይ በማጤን የመዘዋወሪያ አበል እንዲሻሻል አበክረን እናሳስባለን፡፡

## የቢሮ ችግር

57. መ/ቤቱ ከፍተኛ የሆነ የቢሮ ችግር እንዳለበት እና ችግሩን ለመወጣት አዲስ ሕንፃ ማሠራት ወይም ሌላ የመንግሥት ሕንፃ ማግኘት እንዳለበት ባለፉት አመታት በተደጋጋሚ የተገለጸ ሲሆን፣ ምክር ቤቱም ችግሩን ተገንዝቦ በአስፈጻሚው አካል መፍትሔ እንዲፈለግ የጠየቀ ቢሆንም መፍትሔ ሊገኝ አልተቻለም፡፡ በ1999 በጀት ዓመት መ/ቤቱ እየተጠቀመበት ያለውን ህንፃ ለማሳደስ ብር 2 ሚሊዮን በጀት ተፈቅዶ የነበረ ቢሆንም እድሳቱን ለማከናወን የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ የሕንፃ ዲዛይን ባለሥልጣን መ/ቤትን መስፈርት ያሟሉ በቂ ተጫራቾች ባለመቅረባቸው በጀቱን መጠቀም አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ምክር ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መ/ቤቱ ተለዋጭ ሕንፃ እንዲያገኝ፣ ካልሆነም የራሱን ሕንፃ መሥራት እንዲችል ተስማሚ ቦታና በቂ በጀት በማግኘት ረገድ ተገቢው ድጋፍ እንዲሰጥና መ/ቤቱ ከችግሩ እንዲላቀቅ እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

## በሂሣብ ምርመራ ኮርፖሬሽን አልግሎት እና የግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

58. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሰቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት

ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ይሰጣል፡፡

59. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ1998 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 3 ክፍል 3 በዝርዝር ቀርቧል፡፡

## ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

60. በግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በ1998 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉ 301 ሂሣቦች ላይ የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ሲተነተን፤ 115 ሂሳቦች ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean)፣ 138 ሂሳቦች ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Exept for)፣ 47 ሂሳቦች አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል አስተያየት የተሰጠበት (Disclaimer) እና 1 ሂሳብ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse) የተሰጠባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በሌላም በኩል እስከ ሰኔ 30/1998 ዓ.ም መጨረሻ መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ከሶስት ዓመታት በላይ ሂሳባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 40 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ በመሆኑም የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ እነዚህ ድርጅቶች ሂሳባቸውን ዘግተው ኦዲት እንዲያስደርጉ መከታተል ይኖርበታል፡፡

## የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን
## የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች

61. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማው:-

- የመንግሥት ለሆኑ ወይም በአብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት ማበርከት፣
- የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትን ዘዴ መፈለግና አገሪቷ በዚህ ረገድ በአጭር ጊዜ ራሷን እንድትችል ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ጥረት ማድረግ፣

ነው፡፡

## የሥራ ክንውን

62. በዚህ መሠረት በ1998 በጀት ዓመት በነበረው 141 የሰው ኃይል 222 ኦዲቶችን ለማከናወን አቅዶ 240 ኦዲቶችን ወይም ከዕቅዱ በ18 ኦዲቶች ከፍ ያለ ነው::

## የፋይናንስ እንቅስቃሴ

63. ኮርፖሬሽኑ በ1998 በጀት ዓመት ብር 4.4 ሚሊዮን ከኦዲት ሥራ ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 6 ሚሊዮን ገቢ በማስገኘት፣ እንዲሁም ብር 4.8 ሚሊዮን ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 4.8 ሚሊዮን ወጪ በማድረግ ብር 1.2 ሚሊዮን ትርፍ ሊያገኝ ችሏል::

## ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች

64. ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች በርካታ ሲሆኑ በተለየ ጥራዝ በቀረበው ዘገባ በዝርዝር የተጠቀሱ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ፣

- ብዙዎቹ የልማት ድርጅቶች በሥርዓት ተጠንቶ ተግባራዊ የሆነ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ተስማሚ የሂሣብ አያያዝ መመሪያ የሌላቸው መሆኑና ያላቸው ቢኖሩም በአጥጋቢ ሁኔታ በሥራ ላይ አለመዋሉ፣
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎች፣ የሥራ አመራር ቦርድ እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በውጭ ኦዲተሮች በሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዳቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ አለመዝጋታቸውና እንዲዘጉም የሚደረገው ግፊት የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑ፣

ናቸው::

## የኮርፖሬሽኑ ዓበይት ችግሮች

65. ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማዎች አንዱ የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትን ዘዴ መፈለግና ሀገሪቷ በዚህ ረገድ ራሷን እንድትችል ጥረት ማድረግ መሆኑ ቢታወቅም፣ ለባለሙያዎች ስልጠና ቀደም ባሉት ዓመታት ያገኝ የነበረው የገንዘብ ድጋፍ ጨርሶ መቋረጡ በዚህ በኩል የሚጠበቅበትን ድርሻ ሊያበረክት አልቻለም::

66. በሌላም በኩል ድርጅቱ ከሚያገኘው አነስተኛ ገቢ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ በተልዕኮ ትምህርት ያስተማራቸው ባለሙያዎች ለሥራቸው በሚከፈለው

ተመጣጣኝ ያልሆነ ደመወዝ ምክንያት ሥራቸውን እየለቀቁ በላቀ ደመወዝ በግል ድርጅቶች ስለሚቀጠሩ ድርጅቱ ከፍተኛ የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት አጋጥሞታል። ይህን ችግር በማቃለል ድርጅቱ የሚጠናከርበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል።

## ማጠቃለያ፣

67. ከዚህ በላይ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ1998 በጀት ዓመት ያከናወናቸውን ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝቶች፣ በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ውስጥ የታዩትን ችግሮች፣ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሁኔታዎች፣ መ/ቤቱ በአሁኑ ጊዜ ያለበትን ዐበይት ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል። ምክር ቤቱ በ5 ጥራዝ የቀረበለትን ሰፊ ሪፖርት በዝርዝር መርምሮ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ፣ እንዲሁም በሕግ በተሰጠው ተጠያቂነትን የማስፈን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት በመንግሥት አወቃቀር በየደረጃው በሚገኙ አካላት ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ አስፈላጊውን የበላይ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ ስናሳስብ፣ በዚህ ረገድ የምክር ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተጠናክሮ እንዲንቀሳቀስ፣ በተለይም በአሁኑ ጊዜ የሀገሪቱን የአምስት ዓመት ስትራቴጂ እቅድ አፈጻጸም በመከታተልና ድህነትን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ፣ የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በሙሉ መሰብሰቡን፣ የበጀት ወጪ በቁጠባና በትክክል መፈጸሙንና ቁልፍ በሆኑ የልማት ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች አፈፃፀም ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለምክር ቤቱ ከፍተኛ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን በድርጅታዊ አቋም፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል እና በቁሣቁስ እንዲያጠናክር በአጽንኦት እያሳሰብሁ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ።

በመጨረሻም የምክር ቤቱ አፈጉባዔዎች፣ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች እና መላ አባላት በጥሞና ስለአዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።